<u>አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ</u>

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስን (፪)
አመሰግናለሁ በየዘመን (፪)

አንድ ጌታ አንድ አምላክ አንድ አገዛዝ ስልጣን
ከዚህ በቀር ሌላ ምንም አይጨምር
በሦስትነታቸውም በስም በአካል በግብር
በእነዚህ በስተቀር ምንም አይጨምር

አዝ...

በሰማያት ያሉ እልፍ አዕላፋት
መናብርት ሥልጣናት ኃይላት ሊቃናት
ያመሰግናሉ እያሉ በፍቅር
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር

አዝ...

አመሰግናለሁ የተቻለኝን
እኔም እንደነሱ ባልመጣጠን
አመድና ትቢያ ስሆን አከበርከኝ
ስምህን ለመጥራት ይኸው አበቃኸኝ

አዝ...

ይኸው በዚህ ዕለት ከፊትህ ቆሚያለሁ
በመቅደስህ ዙሪያ ስምህን እጠራለሁ
መንበረ ፀባኦት ትድረስ ምስጋናዬ
ያመሰገንኩትም ትቅረብ ከጌታዬ

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org